DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# የደረጃ ሁለት መመሪያ
# Coronavirus2019(COVID-19): ለሆቴሎች እና ለማረፊያ ቦታዎች የሚሆን መመሪያ

በደረጃ ሁለት ወቅት ፣ ህዝብ እና ቢዝነሶች ለሁሉም የተጋላጭነትን እድል ለመቀነስ አዳዲስ ባህሪያትን እና ጠንከር ያሉ የደህንነት እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ :: ይህ ሰነድ በደረጃ ሁለት ወቅት ለሆቴል ማቋቋሚያዎች የታሰበ ነው :: በዚህ ደረጃ፣ የእንግዳ አገልግሎቶች እና ውስን ስብሰባዎች የተፈቀዱ ሲሆኑ እንዲሁም የሆቴል ምግብ ቤቶች የኢንዱስትሪ ደረጃዎችን በጠበቀ ሁኔታ እንዲከፈቱ ተፈቅዶላቸዋል :: የባር እና የምሽት ጭፈራ ቤቶች ተዘግተው የሚቆዩ ይሆናሉ :: **የሆቴል መዋኛ ገንዳዎች እንደተዘጉ ይቆያሉ ::** አገልግሎቶች በሚቀርቡበት ጊዜ **በሠራተኞች ፣ በእንግዶች እና በማህበረሰቡ መካከል የ COVID-19 የስርጭት አደጋን ለመቀነስ እርምጃዎችን መተግበር አለባቸው ::** ለተጨማሪ መረጃ coronavirus.dc.gov/phasetwo ን ይመልከቱ።

እባክዎ ያስተውሉ የ COVID-19 ምልክቶች የሚታዩበት ወይም በቅርብ ጊዜ በ COVID-19 ከተያዘ ሰው ጋር ግኑኝነት ያደረገ ማንኛውም ሰራተኛ ወይም ደንበኛ ፤ ሌሎችንም ለበሽታው የማጋለጥ እድል ስላለው ተቋሙ ውስጥ ለስራ፣ ለቢዝነስ ወይም ለመዝናናት መገኘት የለበትም :: የ COVID-19 ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ: ትኩሳት (በግምት ወይም 100.4 ዲግሪ ፋራናይት) ፣ ብርድ-ብርድ ማለት ፣ ሳል ፣ የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር ፣ ድካም ፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመም ፣ ራስ ምታት ፣ አዲስ የጣዕም ወይም የሽታ ስሜት ማጣት ፣ የጉሮሮ መቁሰል ፣ የአፍንጫ መደፈን ወይም ፈሳሽ፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ ፣ ተቅማጥ ፣ ወይም ደግሞ ጥሩ ያልሆነ የጤና ስሜት።

## ሰራተኞች እና እንግዶች በየቀኑ በሽታውን ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎችን መተግበር አለባቸው

- **ከታመሙ** ወይም በቅርብ ጊዜ በ COVID-19 ከተያዘ ሰዉ ጋር ከተገናኙ **ቤት ይቆዩ**።
- በሚቻልበት ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ቢያንስ የ 6 ጫማ ያህል ርቀትን ይጠብቁ። ከሌሎች ሰዎች ጋር አካላዊ ግንኙነቶችን (መጨባበጥ፣ ሀይ-ፋይቭስ) ማስወገድ።
- ሰራተኞች ከጨርቅ የተሰሩ የፊት መሸፈኛዎችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::
  - ለሠራተኛው መደበኛ ሥራ የመተንፈሻ ቁሳቁሶች ወይም የፊት ጭምብሎች የሚያስፈልጉት ከሆኑ እነዚያ ቁሳቁሶች አሁንም ሊለበሱ ይገባል :: ያለ ቫልቭ ያሉ የመተንፈሻ ቁሳቁሶች የ COVID-19 ስርጭትን ለመከላከል የሚመከሩ ናቸው ::
- እንግዶች ወደ ተቋሙ በሚገቡበት ጊዜ እና በተቋሙ የህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ሲሆኑ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ መልበስ አለባቸው።
- ተደጋጋሚ የእጅ ንጽሕናን ያከናውኑ (በሳሙና እና በውሃ ወይም የአልኮል ይዘት ያለው የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር) ::
  - የእጅ ንፅህናን ለማከናወን ወሳኝ ጊዜዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:
    - ምግብ ከመመገብ በፊት፣
    - መጸዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በኋላ፣
    - የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ከመልበስዎ፣ ከመንካትዎ ወይም ከማዉለቅዎ ወይም ፊትዎን ከመንካትዎ በፊት እና በኋላ፣
    - ከስራ ፈረቃ እና ከስራ ዕረፍት በፊት እና በኋላ፣
    - ለእያንዳንዱ እንግዳ አገልግሎት ከመስጠት በፊት እና በኋላ ፣
    - የእንግዳውን ንብረቶች ከያዙ በኋላ, እና
    - አፍንጫዎን ካፀዱ፣ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ በኋላ።

## ለአሰሪዎች የሚሰጥ አትኩሮት

- አሰሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የሆነ የሥራ ቦታን የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው :: የ COVID-19 የስርጭት አደጋን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ የሥራ ቦታ አደጋዎችን ለመለየት የሥራ ቦታውን በጥልቅ መገምገም ::
- ተደጋጋሚ የእጅ ንጽህና እንዲተገበር (ለምሳሌ: ሳሙና እና ውኃ ወይም 60% የአልኮል ይዘት ያለውን የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር) አቅርቦቶችን ያዘጋጁ :: የእጅ ንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን በሠራተኛ እና በእንግዳ ማረፊያ ቦታዎች (ለምሳሌ ፣ የማስተናገጃ ዴስክ ፣ የሥራ ጣቢያዎች ፣ በእንግዳ መቀበያ ፣ የመሰብሰቢያ ቦታዎች ፣ ወዘተ) ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ::
- ለሠራተኞች ተገቢውን የግል መከላከያ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ: ጭምብሎች ፣ ጓንቶች) እና የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ያቅርቡ :: ጓንት በተለመደው የሥራ ኃላፊነት በተጠቀሰው መሠረት መደረግ አለበት።

- ተገቢውን የፊት መሸፈኛ አጠቃቀምን ፣ የማህበራዊ ርቀትን እና የእጅ ንፅህናን በተቋሙ ሁሉ የሚያበረታታን ምልክት ማሳየት።
- ተለዋዋጭ እና ቅጣትን የማያሳዩ የመልቀቂያ ፖሊሲዎችን ይተግብሩ ፣ እንዲሁም የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ ይፍቀዱ :: የትምህርት ቤት ወይም የሕፃናት መንከባከቢያ ስፍራዎች መዘጋት ያሉባቸው እነደሆነ ፣ ወይም የታመሙ የቤተሰብ አባሎቻቸውን የሚንከባከቡ ከሆነ ከልጆቻቸው ጋር አብረው መቆየት ለሚፈልጉ ሰራተኞች ደግሞ የፈቃድ ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆን አለባቸው::
- የማህበራዊ ርቀትን ለማስጠበቅ በተቻለ መጠን የሰራተኞችን የእረፍት ጊዜዎችን ማፈራረቅ::
- ስለ COVID-19 ተቀጣሪዎቹን ማስተማር:: ለተጨማሪ መረጃ [coronavirus.dc.gov](coronavirus.dc.gov) ይህንን ይጎብኙ::
- ማናቸውም የሚከናወኑ ስብሰባዎች ማጠቃለል የሚችሉት ከብሔራዊ ካፒቶል ክልል የሆኑትን ተሰብሳቢዎች ብቻ ሲሆን እንዲሁም ሠራተኞችን ጨምሮ ከ 50 ግለሰቦች ማስበለጥ የለባቸውም ::
- **የፀጉር ቤት ፣ ሳሎን ፣ ስፖ ፣ ጂም እና የአካል ብቃት ፣ ችርቻሮ ሱቅ ፣ መዝናኛ ፣ ምግብ ቤት ፣ የዝግጅት አዳራሽ ኪራይ ወይም የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ለሚያቀርቡ ተቋማት በ** [coronavirus.dc.gov/phasetwo](coronavirus.dc.gov/phasetwo) ውስጥ ለእያንዳንዳቸው ልዩ መመሪያዎችን ይመልከቱ

## ቅርብ ግንኙነትን ያስወግዱ እና የመነካካት ነጥቦችን ይቀንሱ

- በእንግዶች እና በሠራተኞች መካከል ቢያንስ የ 6 ጫማ ያህል ርቀትን ለማረጋገጥ መተላለፊያዎችን ፣የመስተንግዶ ስፍራዎችን ፣ የተመዝግቦ መግቢያ እና መውጫ ቦታዎችን ፣ የስብሰባ ቦታዎችን ፣ የቢሮ ቦታዎችን ፣ የማረፊያ ክፍሎችን እና ሌሎች የተቋሙ ቦታዎችን ያዘጋጁ :: ይህ ወንበሮችን ማስወገድ ፣ በጠረጴዛዎች እና ወንበሮች መካከል ያለውን ርቀት መጨመር ፣ ወይም ማህበራዊ ርቀት አማራጭ በማይሆንባቸው ስፍራዎች የሚያሳዩ መለያያዎችን ወይም ሌሎች አካላዊ መሰናክሎችን ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል ::
- በመተላለፊያ ስፍራዎች ፣ የተመዝግቦ መግቢያ እና መውጫ ቦታዎችን፣ የታክሲ መስመሮችን ፣ ወዘተ ውስጥ መጨናነቅ እንዳይከሰት ለመከላከል የእይታ ምልክቶችን ይጠቀሙ ::
- በእንግዳ ማረፊያ ክፍሎች እና በሌሎች የተቋሙ አካባቢዎች ሊጸዱ ወይም ከጀርም ነፃ ሊደረጉ የማይችሉ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚነካኩ እቃዎችን (ለምሳሌ ፣ መጽሔቶች ፣ ጋዜጦች ፣ በራሪ ወረቀቶች) ያስወግዱ።
- የቤት አያያዝ አገልግሎቶች እንግዶች በማይኖሩበት ጊዜ መደረግ አለባቸው ፣ እና በተቻለ መጠን ከእንግዶች ዕቃዎች ጋር የሚደረግ ንክኪ መቀነስ አለበት ::
- ያለ ንክኪ የሚደረጉ ተመዝግቦ የመግባትን እና የመውጣት ስርዓቶችን እንዲሁም የዲጂታል መሣሪያ የክፍያ ስርዓቶችን ይተግብሩ ::

## ለበሽታው ምልክቶች ማጣራት እና መከታተል

- በየዕለት ለሰራተኞች፣ ሻጮች፣ ኮንትራክተሮች እና ለማናቸውም ተጨማሪ ሰራተኞች የስራ ፈረቃቸው ከመጀመሩ በፊት ምርመራዎችን (ለምሳሌ: የምልክት መጠይቅ) ማከናወን ::
- ወደ ተቋሙ እንደደረሱ ለእንግዶቹ እና ለጎብኝዎች ምርመራ ያድርጉ ::
- የምርመራ ሂደቶችን ለሠራተኞች እና ለእንግዶች ለማሳወቅ በንግድ ቤቱ መግቢያ ላይ ምልክት ያስቀምጡ ::
- ቢያንስ ለ 30 ቀናት ያህል የተቋሙን አገልግሎቶች ለሚጠቀሙ ግለሰቦች ዕለታዊ መረጃ መዝግበው ይያዙ :: ይህ መረጃ በእርስዎ ተቋም ውስጥ የ COVID-19 ኬዝ የተከሰተ እንደሆነ ፣ የአድራሻ መረጃን ለማግኘት ይረዳል ::
    - የሆቴሉ አስተዳደር በግቢው ውስጥ የነበሩትን የእያንዳንዳቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር መዝግቦ ለማስቀመጥ፣ ሂደት መያዙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት ::
    - ይህም፣ ምንም እንኳን የአንድ ሌሊት እንግዳ ቢሆኑም ፣የዝግጅት ተሳታፊዎችን እና ማናቸውንም የሆቴሉ አገልግሎት ደንበኞችን አጠቃልሎ የሆቴሉ ጎብኝዎችን እና እንግዶችን በሙሉ ይመለከታሉ ፣ (ማለትም የምግብ ቤቶች ፣ ስፓዎች) ::

## ማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ማድረግ

- ተቋሙ ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት እና ከፍተኛ ንክኪ የሚደረግባቸውን ቦታዎች (ለምሳሌ: የማስተናገጃ ዴስክ፣ የእንግዳ መቀበያ ስፍራዎች፣ የእረፍት ክፍሎች፣ የመፀዳጃ ክፍሎች፣ የአሳንሰር መጫኛ ቁልፎች፣ የበር እጀታዎች፣ የሻንጣ ጋሪዎች፣ የፊት ዴስክ እስክሪብቶች፣ ወዘተ) ቀኑን ሙሉ በተደጋጋሚ ለማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ለማድረግ አጠቃላይ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል ::
- ማናቸውም የተጋሩ የሠራተኛ መሣሪየዎች (ለምሳሌ: ስልኮች ፣ ኮምፒተር ፣ ጋሪዎች ፣ ወዘተ) በመደበኛነት በታቀደው የማጽዳት እና ከጀርም ነፃ የማድረግ የጽዳት እና የመፀዳጃ ሂደት ውስጥ ማለፍ እንዲሁም በሠራተኞች መካከል መፅዳት እና ከጀርም ነፃ መደረግ አለበት።
- የቆሸሹ እና ያገለገሉ የአልጋ ልብሶች ከእንግዳ ማረፊያ ከመውጣታቸው በፊት ለአንዴ ጥቅም ላይ በሚውሊ የታሸጉ ከረጢቶች ውስጥ መደረግ አለባቸው ::
- አንድ እንግዳ በሆቴል ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ከታመመ፣ ክፍሉን ለማፅዳት እንግዳዉ ከወጣ በኃላ እስከ 24 ሰዓት ይጠብቁ ::

- በቤት ውስጥ ሠራተኞች እና በእንግዶች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶችን ለመቀነስ ከ 7 ቀናት በታች ላሉት ቆይታዎች የቤት አያያዝ አገልግሎትን አለመስጠት የመሳሰሉ ስትራቴጂዎችን መጠቀም ::
- ስለ ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ስለ ማድረግ እንዲሁም COVID-19 ን የሚያስከትለውን ቫይረስ ለማጥፋት ውጤታማ ስለሆኑ ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረጊያ ምርቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ድረ ገጽን ይመልከቱ: cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/reopen-guidance.html፡፡
- አንድ ሰው በ COVID-19 በሚያዝበት ጊዜ፣ ስለ ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ስለ ማድረግ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ድረ ገጽን ይመልከቱ: cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/disinfecting-building-facility.html፡፡

## የግንባታ አትኩሮቶች

- ሕንፃው ረዘም ላለ ጊዜ ከተዘጋ ፣ የ HVAC ስርዓቶችን ማየትዎን አይርሱ እንዲሁም ሁሉም የውኃ ስርዓቶች ጥቅም ላይ ለመዋል ደህንነታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ለረጅም ጊዜ ከተዘጉ ወይም ከዝቅተኛ የአሰራር ሁኔታ በኃላ ዳግም ለአገልግሎት ስለሚከፈቱ ህንጻዎች የ CDC መመሪያን ይመልከቱ: cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/php/building-water-system.html፡፡

## ለ COVID-19 የመጋለጥ አደጋ ወቅት የሚረዱ እቅዶችን ማዘጋጀት

- አንድ ሰራተኛ ወይም ደንበኛ በ COVID-19 በሚያዝበት አጋጣሚ ወቅት ሊደረጉ ስለሚገባቸው ነገሮች እቅድ ያውጡ፡፡
- በተቋሙ ውስጥ ያለ አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ እና ይህን መረጃ ማሳወቅ ከፈለገ ሊያሳውቅ የሚችልበትን የመገናኛ ስፍራን ለይቶ ማዘጋጀት፡፡
- አንድ ግለሰብ በስራ ላይ እያለ ከላይ ከተጠቀሱት ምልክቶች የትኛውንም ያሳየ እንደሆነ ፣ ያ ግለሰብ ወዲያውኑ ራሱን የሚያገልበት ፣ ለተቆጣጣሪው የሚያሳውቅበት እና ተቋሙን ለቅቆ መውጣት የሚችልበት ሂደት መዘጋጀት አለበት ፡፡
- አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ እንደሆነ ለተቋሙ ለማሳወቅ ከወሰነ፣ ተቋሙ የሚከተሉትን ለሰራተኞቹ ለማጋራት የማሳወቂያ ሂደት ሊኖረው ይገባል:
  - የ COVID-19 ፍንጮችን እና ምልክቶችን ጨምሮ ስለ COVID-19 ትምህርት ይሰጣል
  - ለ COVID-19 የምርመራ ውጤት ፖዘቲቭ ለሆኑ ግለሰቦች የግኑኝነት መረጃ መመሪያ ማየት ከፈለጉ በ coronavirus.dc.gov/healthguidance ላይ ይገኛል፡፡
  - በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ለ COVID-19 ምርመራ አማራጮች መረጃ በ coronavirus.dc.gov/testingይገኛል።
- አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ እንደሆነ ለተቋሙ ካሳወቀ፣ **እና** ሰራተኛው ከደንበኞች/ጎብኝዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት አድርጎ ከነበር ***<u>ወይም</u>*** ደንበኞች/ጎብኝዎች የ COVID-19 የምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ እንደሆነ ለተቋሙ ካሳወቁ፣ ተቋሙ ከሚከተለው መረጃ ጋር በ coronavirus@dc.gov ላይ በኢሜይል ለዲሲ ሄልዝ ማሳወቅ አለበት:
  - በኢሜይል የርዕሰ ጉዳዩ መስመር ላይ "COVID-19 ኮንሳልት"
  - ዲሲ ሄልዝ ጥሪውን ለመመለስ እንዲያስችለዉ በተቋሙ ዉስጥ ጥሩ የሚባል የማግኛ ቦታን ስም እና የቀጥታ ስልክ ቁጥር
  - ተጋልጠዋል ተብለው የሚታሰቡ የደንበኞች / የጎብኝዎችን ግምታዊ ቁጥር
  - ስለ ክስተቱ / ሁኔታው የሚገልጽ አጭር ማጠቃለያ።
- የዲሲ ሄልዝ የምርመራ ባለሙያ በ 48 ሰዓታት ውስጥ በተገቢው መንገድ የቀረቡትን የኢሜል ማስታወቂያዎችን የሚከታተል ይሆናል፡፡

ከዚህ በላይ ያሉት መመሪያዎች ወረርሽኙ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር እየተሻሻሉ የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡ እባክዎን coronavirus.dc.gov ለወቅታዊ መረጃ በመደበኛነት ይጎብኙ።